**የሰፕቴምበር 2014 QuickNotes ዜና መልእክት 2ኛ ቅፅ**

**ነፃ የቤት ስራ እርዳታ እዚህ ይገኛል!**

Homework Hotline Live (የቤት ስራ በአስቸኳይ የቴሌፎን መስመር) (HHL)፣ ከK–12 ለሚገኙ ተማሪዎች ከMCPS መምህራን ነፃ የቤት ስራ እገዛ ለማቅረብ ለ29ኛው ወቅት ለማቅረብ ተሰናድቷል። ተማሪዎች የHHL መምህራንን በቴሌፎን ከ4–6 p.m. መስመር ላይ ከ4–9 p.m. ማክሰኞ፣ ሮብ፣ እና ሀሙስ፣ እንዲሁም ሰኞ ከ6-9 p.m. ማግኘት ይችላሉ።

ተማሪዎች HHLን ለማግኘት በርካታ መንገዶች አሏቸው። ጥያቄዎች በነዚህ በኩል ማቅረብ ይችላሉ፦

- የቴሌፎን ጥሪ በ301-279-3234 በማድረግ
- የHHL ድርጣብያ (AskHHL.org) በመጎብኘት
- የተክስት መልእክት ወደ 724-427-5445 በመላክ
- ኢሜይል ወደ (question@AskHHL.org) በመላክ
- ወደ ፌስቡክ (Facebook) (facebook.com/AskHHL) መልእክት በመለጠፍ
- ወደ AskHHL የKik መልእክት መላክ
- Instagram (AskHHL) ላይ መለጠፍ

HHL ለሚቀርቡለት ጥያቄዎች ከ4 እስከ 9 p.m. መልስ ይሰጣል። ማክሰኞ፣ ሮብ እና ሀሙስ ጥያቄዎች ፊት ለፊት/በቀጥታ በቴሌቭዥን መልስ ይሰጥባቸዋል። በሌላ ወቅት የሚቀርቡ ጥያቄዎች በቴክስት ወይም በኢሜይል መልስ ያገኛሉ።

HHL በMCPS-TV (Comcast 34, Verizon 36, RCN 89) ቴሌቪዥን እና በwww.AskHHL.org ሊታይ ይችላል

ተማሪዎችና ወላጆች ስለHHL ወቅታዊ ዜና በTwitter @AskHHL መከታተል ይችላሉ።

የHHL ድር ጣብያ

**የቤት ስራ፡- ወላጆች እንዴት ማገዝ እንደሚችሉ**

በትምህርት ክፍል የተማሩትን ለመለማመድና የርእስ ፊሬ ነገር ሙሉ በሙሉ ቁጥጥር ስር ለማዋል የቤት ስራ ለተማሪዎች ታላቅ እድል ነው። ለወላጆችም በልጆቻቸው ትምህርት ለመሳተፍ ተጨማሪ እድል ነው። ልጆችን በቤት ስራ ማገዝ ሁልጊዜ ቀላል አይደለም ለተማሪዎች ትርጉም እንዲኖረው ለማድረግም በመምህራን፣ በተማሪዎችና በወላጆች መካከል ትብብርና ግንኙነት ይጠይቃል። ይህ የወላጅ ቼክሊስት (የመቆጣጠርያ ዝርዝር) ልጅዎን መልካም የማጥናት ልምዶች እንዲያዳብር እና የቤት ስራዎቻቸውን በስኬታማነት እንዲፈፅሙ እንዴት ማገዝ እንደሚችሉ የተወሰኑ ጠቃሚ ጥቆማዎች ይሰጣል።

- ✓ **ትምህርትና የቤት ስራዎች አስፈላጊነታቸውን እርስዎ እንደሚያምኑባቸው ያሳዩ።** ይህንንም፣ ለቤት ስራ መደበኛ ግዜ በማስቀመጥ፣ ከልጅዎ ጋር ሆነው ግቦችን በማስቀመጥ፣ ፀጥታማ ቦታ በመምረጥ፣ ስራውን ለመፈፀም የሚያስፈልጉ መገልገያዎችን በማቅረብ ሊያከናውኑ ይችላሉ።

- ✓ **አመራር መስጠት።** ስራውን እርስዎ ራስዎ ሳይሰሩ አመራር ሊሰጡ ይችላሉ! ልጆችዎ ተደራጅተው መጪ ተግባሮቻቸውን እንዲከታተሉ ያግዟቸው፣ ጊዜን እንዴት እንደሚያስተዳድሩና ተግባሮችን እንዲፈፅሙ ያስተምሯቸው፣ የልምምድ ፈተናዎችን ይስጧቸው ለአፈፃፀማቸውም ያድንቋቸው—በትልቁም በትንሹም።

- ✓ MCPS **ለተማሪዎች የሚያቀርባቸውን ነፃ የቤት ስራ መገልገያዎችን ልጅዎ እንዲጠቀምባቸው ያበረታቱ።** ሰፊ የመገልገያዎቹ ዝርዝር፣ እንዲሁም ምን እንደሚያቀርቡ ማብራርያ እዚህ ማግኘት ይችላሉ።

- ✓ **ፕሮብሌሞችን ለመፍታትና እንቅፋቶችን ለመወጣት ከልጅዎ አስተማሪ ጋር አብረው ይስሩ።** ከአስተማሪዎች ጋር ቀጣይ ግንኙነት ወሳኝ ነው። ከያንዳንዳቸው የልጅዎ አስተማሪዎች ጋር ችግሮች ከመከሰታቸው በፊት በአመቱ መጀመርያ ላይ ይነጋገሩ። ስለ ልጅዎ ግስጋሴ ቀጣይ መረጃ እንዲኖርዎ በመምህር-ወላጅ ስብሰባዎችና በትም/ቤቱ በአል ላይ መገኘትዎን ያረጋግጡ። በቤት ስራም ሆነ በት/ቤት ባጠቃላይ ልጅዎ ችግር እንዳለው የሚጠረጥሩ ከሆነ፣ ከአስተማሪው/ዋ ጋር የችግሩን መፍቻ ፕላን ለመቀየስ ቀጠሮ ይጠይቁ።

- ✓ **በEdline በመጠቀም በትምህርት አመት በሞላ የልጅዎን ግስጋሴ ይቆጣጠሩ።** Edline በድር የተመሰረተ የመካከለኛና የከፍተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ወላጆች የልጃቸውን ማርኮችና ስራዎች ለመቆጣጠር የሚያስችል የመገናኛ መሳርያ ነው። ተጨማሪ ጥቅሙ ከመምህራን ጋር ኢሜይል መላላክ ማስቻሉ ነው። Edline ለመጀመር ወይም አገልግሎት ላይ ለማዋል ከልጅዎ ት/ቤት ጋር ይገናኙ።

[የቤት ስራ መገልገያዎች](#)

**የቅዳሜ ት/ቤት ተማሪዎችን ስኬታማ እንዲሆኑ ያግዛል።**

George B. Thomas Learning Academy (ጆርጅ ቢ. ቶማስ ሲንየር የመማርያ አካዴሚ) ሰፕቴምበር 20 የ2014-2015 ወራት የቅዳሜ ት/ቤት ይጀመራል። የቅዳሜ ት/ቤት ተጨማሪ የመማርያ ቀን በማቅረብ የMCPS ተማሪዎች በመሰረታዊ የአካዴሚ ርእሶች ታላቅ እውቀት ለማራመድ የሚያግዝ የአነስተኛ ዋጋ የልዩ ጥናትና ክትትል ፕሮግራም ነው። ተጨማሪ አካዴሚያዊ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች በMontgomery County ዙሪያ ከሚገኙት 12 ቦታዎች አንዱ ላይ ፕሮግራሞችን መከታተል ይችላሉ። ትምህርቶች ሰፕቴምበር 20 ጀምረው ሜይ 2 ያልቃሉ። የምዝገባ ዋጋ Free and Reduced-price Meals (ነፃና የቅናሽ ዋጋ ምግብ) (FARMS) ለሚቀበሉ $30 ነው FARMS ለማይቀበሉ ደግሞ $50 ነው።

[George B. Thomas, Sr. Learning Academy](#)

**የፋይናንሳዊ እርዳታ አውደጥናቶች ለ2ኛ ደረጃ ትም/ቤቶች ተዘጋጅቷል**

ስለ ኮሌጅ እና እንዴት እደሚከፈልበት ማሰብ ጀምረው ከሆነ፣ በተለያዩ የMCPS ከፍተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በፎል ወራት ውስጥ በሚካሄዱት በ[ነፃ የፋይናንሳዊ እርዳታ አውደጥናቶች](#) መማር ይችላሉ። ፋይናንሳዊ እርዳታ ምን እንደሆነ፣ ምን አይነት የፋይናንሳዊ እርዳታዎች እንዳሉ እና ተማሪዎች need-based financial aid (በዕርዳታ ፈላጊነት ላይ የተመሰረተ ፋይናንሳዊ እርዳታ) ማመልከት እንዴት እንደሚችሉ በነዚህ አውደ ጥናቶች ይማራሉ። የመጀመርያው አውደ ጥናት ማክሰኞ፣ ኦክቶበር 7 በSpringbrook High School እንዲከናወን በፕሮግራም ተይዟል። ለተጨማሪ መረጃ ከልጅዎ ት/ቤት ጋር ይገናኙ።

**ቡሊዪንግ (አመፅ/ማሸማቀቅ) በት/ቤቶች ላይ የሚያተኩር ክውነት**

የታውን ሆል የቡሊዪንግ (አመፅ/ማሸማቀቅ) በት/ቤቶች ስብሰባ በሲልቨር ስፕሪንግ እሁድ፣ ሰፕቴምበር 28 ከ2–5 p.m. ይካሄዳል። ነፃው ክውነት የኮምፒውተር ቡሊዪንግ ፣ መከላከል፣ ቡሊ የሚያካሂዱ ልጆች እና የቡሊዪንግ ምልክቶች የመሳሰሉ የተለያዩ ርእሶችን ይወያይባቸዋል።

ፕሮግራሙ፣ Bullying in Schools (ቡሊዩንግ በት/ቤቶች)፣ የሚመራው በMontgomery County Office of Human Rights (የሰብአዊ መብቶች ፅ/ቤት) እና በሞንትጎመሪ ኮሌጅ ነው፣ ለህዝብም ክፍት ነው።

ቁልፍ ተናጋሪው Johnnie Williams III (ጆኒ ዊልያምስ 3ኛ)፣ የብሄራዊ ወጣቶች ተሚጋች፣ ነው። ተሳታፊዎች ከቡሊዩንግ ጋር በተያያዙ ርእሶች ከሂሎት ላላቸው ባለሙያዎች ጥያቄዎች ማቅረብ ይችላሉ። ክውነቱ የሚካሄደው በሲልቨር ስፕሪንግ Silver Spring Civic Center, 1 Veterans Place ነው። ለተጨማሪ መረጃዎች፣ ከCommittee on Hate Violence (የጥላቻ ሁከት ኮሚቴ) ጋር በ240-777-8454 ተገናኙ።

**የትምህርት ቤት Open Houses በአል ለኦክቶበር 13 እንዲከበር ተወስኗል**

እለቱን ያስታውሱ! MCPS፣ ሰኞ፣ ኦክቶበር 13ን፣ የት/ቤቶች ክፍት ቤቶች (open houses) ብሎ ሰይሞታል። ይህ፣ ልጆቻቸውን በመማርያ ክፍል ውስጥ ለመታዘብ፣ ስለትም/ቤቱ ፕሮግራሞች ለመማርና የትም/ቤቱን መምህራኖችና ሰራተኞች ለማግኘት፣ ለወላጆች ትልቅ እድል ነው። ለተጨማሪ መረጃ ከልጅዎ ት/ቤት ያጣሩ።

**MCPS በዜናዎች**

ጥቂት ትርፍ ደቂቃዎች አለዎትን? እንግዲያስ ስለMCPS ወቅታዊ ርእሰ አንቀፆች፣ ቪድዮዎች እና የጋዜጣ መግለጫዎችን ይከታተሉ።

***ቪድዮዎች***

የGreencastle ES የቤተሰብ ገበያ ቀን (Family Market Day) በመቶዎች የሚቆጠሩ ተገኝተዋል
የተማሪ ስኬት—ከMCPS ጋር የትብብር ሽርክና፣ የMontgomery County Recreation Department (የመዝናኛ መምርያ) እና Collaboration Council (የትብብር ምክር ቤት)

***MCPS በዜናዎች***

አዲስ ቦታ በሞንጎመሪ ት/ቤቶች ምዝገባ ሲዳብር
Rosa Parks፣ አዲስ የትምህርት አመት ከአዲስ ቴክኖሎጂ ጋር ይጀምራል
Silver Diner አውቲስቲክ ወጣቶችን ለመርዳት ደረሰ
የTilden አረንጓዴ ቡድን (Greene Team) አካባቢን ከማሻሻል በላይ አልፏል
የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት መምህር የስቴት የአመቱ አስተማሪ የመጨረሻ ተወዳዳሪ ሆኖ/ና ተሰየመ/ች
ት/ቤቶች በአዲስ ዘመናት ለአዲስ አመት ሲከፈቱ የፀጥታ ጥበቃ እርምጃዎች ጨመሩ

***የጋዜጣ መግለጫዎች***

133 የMCPS ተማሪዎች ለብሄራዊ የሽልማት ብቃት ግማሽ የመጨረሻ ተወዳዳሪዎች (Semifinalists) ተብለው ተሰየሙ
የJohn Poole Middle School መምህር ለስቴት የአመቱ አስተማሪ የመጨረሻ ተወዳዳሪ

***ሌሎች ታሪኮች***

*[የወቅቱ በመገስገስ/በመዉጣት ላይ የምትገኘው የአምቱ ኮከብ አስተማሪ ዴቦራ ዩንን ይገናኙ]*

**በተማሪ ዲሲፕሊን መመርያ የቀረቡ ክለሳዎች ላይ አስተያየት መስጠት**

የMontgomery County የትምህርት ቦርድ በPolicy JGA፣ *የተማሪ ዲሲፕሊን* በቀረቡት ክለሳዎች ላይ የህዝብ አስተያየት በመሻት ለይ ይገኛል። ይህ መመርያ ከአዲሱ የስቴት ደንቦች ጋር ለማጣጣም ተሻሽሏል ሰላማዊ፣ አወንታዊና መከባበር ለሰፈነበት የመማርያ አካባቢ ቦርዱ የገባበት ግዴታንም ያረጋግጣል፤ የተማሪን ተመስጦ/ትኩረትና ግኙት ይጨምራል፣ እናም የተማሪን መጥፎ ስነምግባር ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት ይከላከላል።
የPolicy JGA ክለሳዎች በዩ. ኤስ. የትምህርት መምርያ እና በዩ. ኤስ. የፍትህ መምርያ በቅርቡ ወጪ ከተደረጉ የት/ቤት ዲሲፕሊን መመርያዎችም ጋር ተስተካክለዋል።

የ*ረቂቅ መመርያ* ቅጂ በMCPS *ድር ጣብያ* ይገኛል ወይም የMCPS የህዝብ ማስታወቂያና የድር አገልግሎቶች በ301-279-3391 በመደወል ሊገኝ ይችላል።

አስተያየት መስጠት የሚፈልጉ ግለሰቦች እስከ አርብ፣ ኦክቶበር 24 በፅሁፍ ማቅረብ ይችላሉ። ሁሉም የፅሁፍ መልሶች ለት/ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ ፅ/ቤት በOffice of the Superintendent of Schools, 850 Hungerford Dr., Room 122, Rockville, Maryland 20850 ወይም በኢሜይል ለየትምህርት ቦርድ መላክ አለባቸው።

ሁሉም መልሶች የትምህርት ቦርድና የት/ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ እንዲጋሯቸው ይደረጋል።

**እንዳይረሱ…**

በሰመር ወራት ስለተከናወነ የአገልግሎት ሰነዳቸውን ተማሪዎች MCPS Form 560-51: Student Service Learning Activity Verification (የተማሪ የትምህርት አገልግሎት እንቅስቃሴ ማረጋገጫ) በመጠቀም እስከ አርብ መስከረም 26 ገቢ ማድረግ አለባቸው። የአገልግሎት ሰአቶች በመጀመርያ ሩብ አመት ሪፖርት ካርድ ይንፀባረቃሉ።

MCPS Form 560-50 በመጠቀም SSL በቅድሚያ እንዲፀድቅ የጠየቁ ተማሪዎች ሰነድ ሲያስገቡ የቅድሚያ ማፅደቂያ ቅፅ ከማስመስከርያ ቅጽ ጋር ማያያዝ አለባቸው። ጥያቄዎች? SSL *ድር ጣብያ* ይጎብኙ።

በፈቃደኛነት በመቅረብና ሙያዎች ከተማሪዎችና ከቤተሰቦች ጋር በመጋራት በMCPS ተማሪዎች ህይወቶች ለውጥ ማስከተል ይችላሉ። በስራ ቀን (Career Day) ከመገኘት የመስክ ጉዞዎችና

የስራ ላይ ስልጠና እስከ ማቅረብ፣ መማርን ህይወት ልትዘሩበት ትችላላችሁ። ዛሬውኑ ለመመዝገብ Connection Resource Bank (የግንኙነት መገልገያ ባንክ) ጋር ይገናኙ።

የመጀመርያ የልዩ ትምህርት አማካሪ ኮሚቴ (Special Education Advisory Committee) ስብሰባ ሀሙስ፣ ሰፕቴምበር 18 2014 ከ7–9 p.m በCarver Educational Services Center, 850 Hungerford Drive in Rockville ይካሄዳል። የልዩ ትምህርት ወላጆች እንዲገኙ በጥብቅ ይበረታታሉ። የልጅ እንክብካቤ ይቀርባል።

**ታላላቅ ት/ቤቶች፣ ተማሪዎች እና ሰራተኞች**

መልካም እድል ለJane Lindsay (ጄን ሊንድሰይ)፣ ወቅታዊዋ የMCPS የአመቱ አስተማሪ፣ ለሜሪላንድ የአመቱ አስተማሪ ስትወዳደር!